የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር/ Ref.No. 63/0059/14
ቀን/Date ጥቅምት 24 2014

**የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ**
**<u>በያሉበት</u>**

**ጉዳዩ፡- <u>ለግብርና አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች ይመለከታል</u>**

ከገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ማኢ.30/7/1789 በቀን 12/02/2014 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በየጊዜው በሚኖረው የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት የግብርናውን ዘርፍ ለማበረታታት ለግብርና አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች ከውጭ ሲገቡ ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ፈቅዷል፡፡

በዚሁ መሰረት ከግብርና ሚኒስቴር የድጋፍ ደብዳቤ ሲቀርብ አስፈላጊውን የጉምሩክ ስነ ስርዓት በመፈፀም አገልግሎት እንዲያገኙ እያሳሰብን ለአፈፃፀም ይረዳችሁ ዘንድ ከሚ/ር መ/ቤቱ የተላከውን ደብዳቤ ቅጂ (02) ገፅ በተቋሙ መረጃ ስርዓት (Local Share ቁጥር <u>\\10.12.0.8/Tariff Classification & Origin/Tariff Classification/</u> የታሪፍ ማሻሻያዎች/ ከመስከረም 01፧2014 ዓ.ም በኋላ የመጡ የታሪፍ ማሻሻያዎች ሳጥን ውስጥ **<u>ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የተፈቀዱ የግብርና ግብዓቶች ዝርዝር</u>**" በሚል ስም የተቀመጠ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**ከሠላምታ ጋር**

ካሣዬ አየለ ሞላ
የታሪፍ ምደባና ስሪት አገር አወሳሰን
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተወካይ

**<u>ግልባጭ፡-</u>**

- ለጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለጉምሩክ ኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍ ምደባ ፖሊሲ ጥናትና ትንተና ቡድን
- ለታሪፍ ምዳባ አሰራርና ድጋፍ ቡድን

**<u>የጉምሩክ ኮሚሽን</u>**

- ለኢትዮጵያ ጉምሩክ አስተላላፊዎች የሙያ ማህበር
- ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

**<u>አዲስ አበባ</u>**



ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
Email: hocrecordopr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia
ፖ.ሳ.ቁ. 2559

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF FINANCE

ቁጥር [illegible]
Ref. No

ቀን 12/2/17
Date

ለገቢዎች ሚኒስቴር

ለጉምሩክ ኮሚሽን

<u>አዲስ አበባ</u>

መንግሥት የግብርና ዘርፉን ለማበረታታት የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰደ እንደሚገኝ የሚታወቅ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ በግብርና ሚኒስቴር ተለይተው የቀረቡ ለዘርፉ የሚውሉ ግብዓቶች ከውጭ ሲገቡም ሆነ በአገር ውስጥ ተመርተው ግብይት ሲፈፀምባቸው ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ መደረጉ ይታወሳል።

ስለሆነም ከዚህ ጋር ተያይዞ በተላከው አንድ ገጽ ሰነድ ላይ የተመለከቱት ለዘርፉ በግብዓትነት እንደሚያስፈልጉ ስለታመነባቸው የግብርና ሚኒስቴር በሚሰጠው ድጋፍ መሰረት ከውጭ ሲገቡ ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ የተወሰነ መሆኑን እየገለጽን፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አፈፃፀሙን በሚመለከት በመከታተል ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት እንዲያቀርብ እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር

ኢዮብ ተካልኝ (ዶ/
ሚኒስትር ዴኤታ

